የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 82 ቁጥር 4(970)

"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።" (ቲቶ 2፥11-13)

ንቁ! ጌታ ይመጣል፥ ተጠበቁ!

(በሚሐርና በአውን)

ቅዱስ መንፈስ የቀደሙ ጸሐፊዎችን በማነቃቃት በሙላቱ እንዲጽፉ ያደረጋቸው የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከላይ አምስት መልእክቶቻቸው አንዱ ስለ ጌታ ዳግም ምጽአት የሚያሳስብ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትኑና ተጠበቁ ብሎ ያስተማረን ስለ ዳግም ምጽአቱ እንድንዘጋጅና እንድንቀደስ ነው። የታመኑት ሐዋርያቱ ንስሐ የገቡ አማኞችን ተጠብቀው ሕይወታቸውን እንዲቀጥሉ ያስተማሩት በቅድስና የጌታን ዳግም ምጽአት እንዲጠብቁ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱሳችን የመንፈሳዊነትና የቅድስና አስፈላጊነት ከዳግም ምጽአቱ በበለጠ የሚያስተምር የለም። *"ጌታችሁ በምን ሰዓት እንደመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ" (ማቴ.24፥42) "የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃቸኋልና" (1 ተሰ.5፥2)*

"ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁ በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ" (1 ጴጥ.1፥13)

<u>ተቀደሱ፥ ትጉ፥ ንስሐ ግቡ!</u>

"እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠው ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም (የሐዋ.3፥21)

"ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል" በዚህም በዘማዊና በኃጢያተኛ ትውልድ መካከል በአኔና በቃሉ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ ዳግም በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ይፍርበታል" (ማር.8፥38)

"ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል ወይስ ሰው ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል? (ማቴ.16፥26) ለሁሉ እንደሥራው ይስረክበዋል።

"ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ" (ቆላ.3፥4)

"ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን ለሚያሳያቸሁ መከራን መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት እድርጎ እንደመልስ ይበቀላል" (2 ተሰ.1፥7

<u>በመጨረሻው ዘመን በብርቱ እንትጋ</u>

(መልእክት ከእስተማሚዎቹ በሬች ካርማይክል)

"ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል። እንግዲህ እንደባለአእምሮ አስቡ ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ" (1ጴጥ.4፥7)

ይህ ጊዜ በትክክል የመጨረሻው የጌታ ዳግም ምጽአት ወቅት ስለሆነ በብርቱ ነቅተን ልንጸልይ ይገባናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው የማይሻር መልእክት ነው፤ *"ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሳልና ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ሰፍራ ይሆናል እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው (ማቴ.24፥7)*

ከዚህ በመቀጥልም በመጨረሻው ዘመን የሚነሰቱትን ስደት ጥላቻና ሥርዓት የጎደለው ኑሮና የብዙዎች ፍቅር መቀዝቀዝና መጥፋትን ያስተምራል። በዛሬው ዘመናችን እነዚህ መልክቶችን በዓለም ዙሪያ በቅርባችን ሳይቀር በማየት በመስማት ላይ እንገኛለን።

ስለዚህ ይህን በእርኩሰት ሁሉ ጥግ የጥላቻ ሁሉ ከፍታ የቅድስና ሁሉ ተገዳዳሪ ድርጊት እያየንና እየሰማን የተቀደሰውን እነዚህን ክፋቶችን የሚሸር የወንጌል ቃል ሳንመሰክር ብንገኝ ምንኛ አሳዛኝ እንሆናለን። እንመለስ ቅድስናና ፍቅርን እንለበስ "ከፍቅርና ከመልካም ሥራ እንድንነቃቃ ይህን አድርጉ" (ዕብ. 10፥24)

<u>የተርጓሚው ወቅታዊ ሀገራዊ መልዕክት ለኢትዮጵያ</u>

ፓስተር/ቄስ ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ

አማዛ ነብራስካ አሜሪካ

"የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅረቡ። የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነጻ ነበራችሁና። እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና። " (ሮሜ.6፥20)

ከኃጢአት ባርነት የወጣን ያንን ባርነት በማንም የሰው ዘር ላይ ማድረግ መመኘት ፈጽሞ አይገባንም። በሀገራችን በአንዳንዶች ላይ በነበረ የመንፈሳዊና የስጋዊ ባርነት በደልን መካድ መርሳት አይቻልም። ሆኖም ግን ያንን ባርነት ዛሬ በሌሎች ላይ በእንደበትና በተግባር

መፈፀምን ከሚፈጽሙት ጋር መተባበር የበፋ ፍርድ ያመጣልና እንመክሰ፣ እንናዘዝ።

ስለዚህ በተጠራንበት የጽርነት ወንጌል ከባርነት ሀሳቦችና ስራዎች አራሳችንንም ሆነ የሚሰሙንን ልንጠብቅ ኃላፊነት አለብን።

በግራም በቀኝም በማንም ሰው ባርነትን ከሚጭኑ በተለይ የጌታን ስም ከሚጠሩ ተለይተን እንቀደስ እንሰማራ።

ክርስቶስ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል

(በጎርጅን)

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቁልጭ ብሎ እንደሚገለጽ ሁኔታዎች እየመሰከሩ ባሉበት ወቅት ላይ ነን። ጌታ እንደሚመለስ ምንም ጥርጥር ባይኖርም መቼ እንደሚመለስ ግን በትክክል ማንም አያውቅም ሆኖም ግን ጌታ በትክክል እንዲመለስ እንደቃሉ የታመነ ነው።

"ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንደምታዩት እንዲሁ ይመለሳል" (የሐዋ.1÷11)

ጌታ በመላእክት ታጅቦ በክብር እንደሚመለስ አራሱም ጌታችንም ሆነ ሐዋርያቱ የጻፉልን የምናምንበት የዳግም ምጽአቱ ማረጋገጫ ነው (1ተሰ.4÷16፣ ዮሐ.14÷3)

ማራናታ ጌታ ሆይ ቶሎ ና (ራእ.22÷20)

ጌታችን አራሱ በድንቅ በታምራት በመላእክቱ ዘማና ደወል በክብር ይመለሳል። የሰዎች አይን ሁሉ እያዩት ጌታችን ስለሚመለስ እኛ አማኞች እንደተሰጠን የተሰፋ ቃል በቃልና በጸሎት ተሞልተን ብንጠብቀው ራሳችንን ከሞት ከውርደትና ከፍርድ እናተርፋለን። ይህን በሚገባ በማድረጋችንም በረከቱን ይጨምርልናል እንጂ የሚጎድን እንደት ነገር የለውም። የጌታችንን መገለጥ ስንጠብቅ እንድም በረከቱ አይጐድልብንም (1ቆሮ.1÷7)

ጌታችን ባረገበት ወቅት ወደ ሰማይ ሲወጣ ደመና እንደተቀበለው ሲመለስም እንዲሁ በደመና ይገለጣል ይመለሳል ልጅቹን በህይወት ያሉትን ይወስዳል፣ ቀድሞ ያንቀላፉትንም በትንሣኤ በክብር ይሰበስባል (1ተሰ.4÷16፣ ሐዋ.1÷9፣ራእ.1÷7)

የጌታችን ዳግም ምጽአት ልክ እንደሙሽራና ሙሽራይቱ ቤተክርስቲያንን (የአማኞችን ጎብረት) እንደሚወስድ የተገለጸልን ትልቁ የበጉ ሰርግ የመጨረሻው ው የተሰፋው ዘላለማዊ ትንቢት ፍጻሜ ነው (ኤፌን 5÷25፣ ራእይ 19÷7)

በመጨረሻው ቀን ጌታችን በስሙ አምነው የዳኑትንና የጸኑትን እንደሚሰበስብ የተጻፈልን ቃል የማይከወት የጸና የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ልንታመንበትና በተሰፋ ልንጠብቀው ይገባል። መች እንደሆነ ባናውቅም ምልክቶቹ ሁሉም በመታየትና በመፈጸም ላይ ስለሆኑ የጌታ ዳግም ምጽአት የሕይወታችን ዋነኛ አጀንዳ አድርገን በቅድስና እንጠብቀው (ኩቃ.12÷35)

የቤተክርስቲያን ተልእኮ በዓለማችን

(በአዩልፍ ሳፊር)

እንግዲህ ሊዲና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ አናንተ ጋር ነኝ (ማቴ.28÷19-20)

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ተወካይና የክርስቶስ ሥራዎች መቀጥያ ሥፍራና ተቋም ወይም ጎብረት ነች።

ጌታችን ከዚህ በኋላ በዓለም እንደማይቀጥል ሐዋርያቱ ግን እንደሚቀጥሉ የተናገረው በሐዋርያቱ ፈለግ ወንጌልን ከምናምነው ከእኛ አማኞች ሁሉ የተሰጠ አደራና ኃላፊነት ነው (ዮሐ.17÷11)

ከክርስቶስ ቃልና መንፈስ የተለየ ጎብረት ወይም ተቋም ቤተክርስቲያን ሊባል የማይችል ነው። ቤተክርስቲያንም ከክርስቶስ መንፈስና ቃል ውጭ በመለየት እንዳች በጎ ነገርየወንጌል ተስፋ ቃል መስጠት አይቻላትም። ጌታችን እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ሕይወትም መንገድም ነኝ።

ያለውን በመከተል ቤተክርስቲያን የአማኞች ማህበረሰብ በክፋት በጥላቻ በኃጢአት መላጀው ግራ ከተጋባና ወደ ገሃነም ገደል የሚነዳውን ማትረፍ የምትችለው በክርስቶስ ብቻ ነው (ዮሐ.14÷6፣ 8÷12 ፣17÷3)

ቤተክርስቲያንና ዓለም በግብ የተለያዩ ቢሆኑም በክርስቶስ ቃል ብርሃን ዓለም ከሞትና ከጨለማ የምትድነው በክርስቶስ ወንጌል ብቻ ይሆናል። አሮጌው አዳም የዘላለም ሞትን ወደ ዓለም እንዳስገባ አዲሱ አዳም ክርስቶስ ደግሞ ሞትን በመስራውና በትንሳኤው ሽሮ የዘላለም ሕይወትን በዓለም ላለነው ሁሉ አስገብቶናልና በእምነትና በሥራ ይህን ዘላለማዊ ተስፋ እንጠብቅ (ዮሐ.3÷16፣ 1ቆሮ.15÷47)

እንግዲህ ባለንበት ቀበሌ፣ መንደር፣ ክልል፣ ስቴት፣ ግዛት፣ አህጉር፣ የክርስቶስ ብርሃን በእኛ እንደገባልን ተስፋ እንዲሰጥና በጨለማ ላሉት ከሞት ከገሀነም መውጫውን እንድናሳይ በቅዱስ መንፈሱ እንቀጣጠል እንበራ!!

የዕለቱን ሥራና አገልግሎት በማየታችን ከመጀመራችን በፊት ዕለቱን የሰጠንን የሚባርከውን ጌታ በጸሎትና በቃሉ እንየው

(በሩት ፓክሰን)

የዘላለም ሰማያዊ አባት ሆይ! አንተ የማትተኛ የማታንቀላፋ ዘወትር ሕዝብህን ስለምትጠብቅ አመሰግንሃለሁ። የሰጠህን ጊዜና ሕይወት ካንተ ይልቅ የተነሣ ነውና እንጠቀምበት ዘንድ የቆሸሸ አእምሮአችንና ልቦችንን እንጸልን ቀድሰን ምሕረትህም አይለየን።

በዛሬዋ ቀን በተለያየ ችግር ውስጥ ያሉትን ልጅችህን በመልካምነትህ ድረስላቸው። ተስፋ መቁረጥና ደካም እንደይመጣብኝ ጠብቀኝ በቅዱስ መንፈስህ ዘወትር

አንቃኝ። በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ለሚያልፉት በቃል በጸሎትና በሚያስፈልጋቸው መደገፍ አንድችል ነበረንትህ አታቋርጠኝ።

ሕይወቴ፣ ቤተሰቤና የምኖርብት ነተማና ሀገር በቅዱስ መጽሐፍ አንደተጻፈው የበረከት ሥፍራ ይሁኑ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተን አመስል ጸሎቴንና መስጋናዬን በክርስቶስ ስም ተቀበለኝ አሜን።

በልብ መዋለልን ምንጭ በማወቅ ፈውስ ከጌታ አንፈልግ

(በዮርዙ ዋትሰን)

"ሰለዚህ አንደቆመ የሚመሰለው አንደይወድቅ ይጠንቀቅ" (1ቆሮ.10÷12)

"በሰው ልጅም ፊት ለመቆም አንድትችሉ ሰትጸልዩ ሁልጊዜ ትጉ" (ሉቃ.21÷36)

ልባችን ከጌታ መለየት ሲጀምር ሳይታወቀን በድንዛዜ በቅዱስ ቃሉ ከተበረትና ከጸሎት ሕይወት መራቅ ይጀምራል።

ጥቃቅን የሚመስሉ የዝናብ ነጠብጣቦች ትልቁን ደፍ ዝናብ በሂደት አንደሚያስነትሉ ሁሉ ጥቃቅን የመሳሰሉ ትኩረት ያላገኙ ወይም በንስሐ ያላስወገድናቸው አርሞች አየገዘፉ ሕይወታችንን ከጌታ ኪለዩ ስለሚችሉ አንዳናቃልላቸው ጌታ በቅዱስ ቃሉ ያሳስበናል÷- *"አንሚጆች ጉልበቱን በሉት አርሱም አላወቀም፣ ሸበትም ወጣበት አርሱም አላወቀም" (ሆሴ.7÷9)*

ልባችን አየዋለለ ከጌታ ልንለይ የምችልባቸውን ጉዳዮች ዛሬውኑ በቅዱስ ቃሉና በልባዊ ንስሐ አናስወግዳለን። ያለመታዘዝ፣ ገዳብ ያለፈ ነጻነት፣ ከጌታ ይልቅ በራስ መታመን የምቶት ኑሮና በይሆናል በዘፈቀደ ሕይወትን መምራት ልባችን አንዲዋሸቅ ያደርጋሉና፣ አንጸየፋቸው፣ ከጌታም አናሳውቅ። (ሉቃ.21÷34)

የሚዋልል ልባችንን መጠበቂያ ምክሮች

በአራስ መታመንና ከጌታ የሚለዩ ልምምዶችና ክፉ ባልንጀርነት ሰዎች ከጌታ ይለያሉ። በተለይ ደግሞ ከሽል ሕይወታችን ለልጅቻችንና ለቤተሰባችን በተሰጠን ጸጋ የመጀመሪያው ቀን ምክር ፈላጊዎች የራሳቸው የልብ በኃጢአት በመሳብ የራሳቸውን ምኞት ብቻ ማራመድ ትልቅ ውድቀት ነው።

አግዚአብሔር በሚከብርበት ሕይወት አንድንገኝ ከራስ ወዳድነት አንድንወጣ መነሻ ሚሆነን የራሳችን ኃጢአት በቅዱስ ቃሉ ታውቆን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስንናዘዝ ነው። (ሮሜ.2÷4)

ከአግዚአብሔር ጋር ስለመስማማት

ከአግዚአብሔር ከፈጣሪያችን ጋር ለመስማማት ብቸኛው መንገድ በቀላሉ በሕጉ መሠረት ኪመጣ ካለው ፍርድ ለመዳ አግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰጠንን የምሕረት ጸጋ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መቀበልና መለማመድ ነው።

ወደ ጌታ በመመለስ የአግዚአብሔር ልጅነትን በመቀበል በቅዱስ መጽሐፍ የተዘረዘሩልንን አሰደናቂ የአግዚአብሔር በረከቶች መቀበል አንችላለን። *"በኃጢአትህ ወድቀሃልና ወደ አምላክህ ወደ አግዚአብሔር ተመለስ" (ሆሴ.14÷1)*

በኃጢአት ማዘን ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ልዩ ተስፋን ያስጨብጣል

በቅዱስ መጽሐፍ አንደተጻፈልን የአግዚአብሔር መንፈስ በቅዱስ ቃሉ ሲመክረን ሲያቀናን ኃጢያታችንን መናዘዛችን ተስፋ በመቁረጥ ወደ ውድቀት መሄድ ሳይሆን በአዲስ ተስፋ ከወደቅንበት መነሣትና ወደ አግዚአብሔር በረከት ወደ ፍትህ መግባትን ያቀዳጀናል። (መዝ.43÷5፣ ኩቃ.18÷1)

ክርስቲያኖች በሚያጋጥማቸው መከራና ፈተና ውስጥ ሁሉ የሚያሳልፍ የሚያሻግር የአግዚአብሔር የተስፋ መንፈስ ይገኛል። (መዝ.43÷5)

አግዚአብሔር በምንም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን አንደተጣልን አንድንቆይ ከቶ ስለማይፈልግ አፅናኝ አበረታች ደጋፊዎቹን ይልክልናል(2 ቆሮ. 7÷6)።

ከሰው አአምሮ ባይመችም አግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በሕይወታችን አንዲከናወኑ የሚፈቅደው ለበጎ ነው (ሮሜ.8÷28)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ የተሰቀለውና የሞተልን በትንሳኤው ሞትን ያሸነፈልን አኛን ከመከራ ኪያወጣን ነው (1ጴጥ.4÷1) ጌታ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ያለን ስለሚያውቀውና ስለሚያሳልፈን ነው።

የጌታ መልአክት ለልብ ፈውስ ነው

ልባችን ነደረሰበት ስቃይ ወይም ሀመም ኪፈወስ የሚችለው ከጌታ በጸሎት በምናገኘው መልስ ብቻ መሆኑን የመበከቷ ታሪክ ያስረደናል (ኩቃስ 18÷1)

በሕይወታችን ፍትህ ያላገኘንባቸው የግል የቤተሰብና የሀገር ጉዳዮችን ተሸክመን ስንኖር መፍትሄውን ከማግኘት ወደ ጌታ ጸሎታችንና ምልጅችን ታክቶን ሰልችቶን ኪቀም ኪደክም ፈጽሞ አይገባም።

ያለመታከት ያንን ክፉ ምድራዊ ደኛ የጠየቀች መበለት ሴት ፍትህ ላገኘች ከመልካሙ ጌታና ፈጣሪ አንዴት ፍትህ አናገኝም?

በጸሎትና በምልጅችን ጸንተን ብንገኝ የጌታ ምሕረት መልስና በረከት በትክክል አንደምንቀበል ቅዱስ የአግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል። *"አኔ ግን ወደ አግዚአብሔር አመለክታለሁ፤ የመድኃኒቴንም አምላክ ተሰፋ አደርጋለሁ አምላኬም ይሰማኛል። ጠላቴ ሆይ ብወድቅ አነሳለሁና በጨለማ ብቀመጥ አግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በአኔ ላይ ደስ አይበልህ"* (ሚኪ.7÷7)

ከተሳካ መንፈሳዊ ሕይወት የልባችን ሃሳብ መቃኘት ወሳኝ ነው

በሃሳባችንና በልባችን ከመሳት ከመውደቅ የበለጠ ክፉ ነገር የለም። ልባችን የተሞላውን በአፍ እንደሚወጣና ታጢአት፣ ክፋት፣ አርኩሰትና ውድቀት እንደሚከተል ቅዱስ ቃሉና የሕይወታችን ልማድ ያስተምሩናል፣ ያረጋግጡልንማል።

ክፉ ሃሳብ ከልባችን እንዲጠፋ እንዲወገድ ብቸኛው መፍትሔ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቅን፣ ደግ፣ ዘላለማዊ ንጹህ ሃሳብ መሞላት ይሆናል (ማቴ.28÷18፣ ዮሐ.14÷15፣ ሐዋ.17÷24)

የጌታችን ቃላትና ትእዛዛት ከሕይወታችን መመሪያዎች፣ ከኑሮአችን ሰነቶ አመልካቾች ናቸውና እንጠቀምባቸው።

በእግዚአብሔር ጥልቅ ዘላለማዊ ቅዱስ ቃል ስንሞላ ጀሮአችን አይናችንና ስሜታችን ሁሉ ለክፉ ጠፊ ዓለም የተዘጋ ይሆናል።

በሁለት ሃሳብ የሚያነክሱ ወይም ለሁለት ጌቶች የሚያገለግሉ ሁለቱንም ያጣሉ። የሚገዙትን፣ የሚሰርቁትን፣ የሚያቃልሉትን የክፉ ሰይጣን ትርክት አምቢ ብለን የጽኑን የላለማዊ ጌታ ቃል ብቻ እንስማ።

የጌታን ሀሳብና ተስፋ ይዘን እንገኝ፣ በመጨረሻው ቀን ጌታችን በአርሱ አምነው የዳኑትን እንደሚሰበስብ የተሻፈልንን የእውነት ቃል የሚይከወጠውን የሚያሻረውን ተስፋ ልንጠብቀውና ልንታመንበት ይገባል።

የጌታ ደግም ምፅአት ምልክቶች በሚገባ በመታየትና በመፈጸም ላይ ባሉበት ዘመን ስለሆንን የጌታን ደግም ምጽአት መጠበቅ የሕይወታችን ዋና ክፍል ይሁን (ኩቃ.12÷35)።

የጸሎት አርበኞች ምክሮች ለአማኞች

የክርስቲያን ሕይወት የሚያደልጥ ዳገት ላይ መራመድን ይመስላል። በጽናትና በተስፋ የሚኖር ክርስቲያን ወድቆ አይቀርም። ይነሳል፣ ሲራመድ በጥንቃቄ በአምላኩ ተማምኖ ከመውደቅ ይድናል (በቻርለስ ስፐርጅን)።

የአገልግሎታችን የስብከታችን የምስክርነታችን ስፋትን ፍሬ በጸሎት ሕይወታችን ይወሰናል። አንዳንዱ ይበልጠትካችኋል ከምኑም ታገኙማላችሁ ያለው የጌታችን ቃል ሁሌም የታመነና በሚያምኑት ሕይወት የሚሠራ ነው (ማቴ.7÷7)

በዚህ ምድር ላይ ሰይጣን አጅግ የሚይወደው ዓለምና ስጋም አንቅፋት የሚፈጥሩበት የጸሎት ሕይወት ነው።

ከብዙይ ኪዳን የአመነት በኑሮች አስነ አዲስ ኪዳን የወንጌልና የትንሳኤው ምስክሮች ድረስ የጌታ ታምራትና ማዳኑ የተከሰተው የእግዚአብሔር መንፈስ በመራው የቅዱሳን ጸሎት ትጋት ነው፣ ዛሬም ያው ነው። (ዘጸ.33÷18፣ ማር.5÷23፣ 1ሳሙ.1÷11፣ ሐዋ.12÷5፣ ዕብ.13÷8፣ ሐዋ.1÷6)

በሀገራችን ኢትዮጵያም በጸሎት በምሳሳ የጌታ ምሕረት ሕዝባችንን የታደገባቸው ጊዜያትን ከመጽሐፍም ሆነ በራሱ ሕይወት ማየቱን ተርጓሚው ምስክር ነው።

ባለፉት ዘመናትም ሆነ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር የማዳን አጅ መቼም አላጠረም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር በረከቱን አንድንቀበል ምህረቱን አንናገኝ የሰጠንን የጸሎት ስጦታ ችላ በማለታችን በመግፋታችን ወደ መቅረቶችን ተወስዶ አፈርን።

በቀደሙ ጊዜያት ታላላቅ መንፈሳዊ አንቅስቃሴዎች የታዩባቸው አንደ ወወክማ፣ YMCAና የመሳሰሉት መንፈሳዊ ተቋማት በባለማዊ ሀሳብ አየተሞሉ የእግዚአብሔር ብርቱ ክንድ ተከያቸው። ድሮ ብዙ መቶ ሺዎች ከአርኩሰትና ከጥፋት የተመለሱባቸው አብያተ ክርስቲያናት ባዶ ሙዚየም ሆነው የቀሩት የጌታን ፊት መፈለጊያ መሆናቸው ቀርቶ በታይታ በባለማውያን በመሞላታችን ነው። (ማቴ.21÷13)

ስለዚህ ዛሬ እንመለስ ቤቱ የጸሎት ቤት ይባላል ያለውን ጌታ እንስማ፣ እንነበል።

ከመንፈሳዊ መነቃቃት እንጸልይ

(በቻርለስ ስፐርጂን)

"አቤቱ ትመለሳለህ ታድነንማለህ ሕዝቡንም በአንተ ደስ ይሉቸዋል" *(መዝ.85÷6)*

ስለ ጸሎት ከመስበክ በስብከት መጸለይ ወይም ጸሎትን መስበክ አጅግ ይበልጣል። መዝሙረኛው ንጉስ ዳዊት ጌታን ትመለሳለህ ታነቃቃናለህ ብሎ አልሰበከም፤ ጸለየ እንጂ።

ይህንን የጸሎት ክፍል የሆነ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስናጠና እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ሕዝቡን የታደገበት፣ የመለሰበት፣ የባረከበትና ያሻገረበትን ዘመን እናስባለን። ሙሴ እና ንጉስ ዳዊት አባቶቻቸው ከግብጽ ባርነት፣ ከባቢሎን ምርኮ፣ ከነከዳውያንና ከተለያዩ ክፉ የእግዚአብሔር ሕዝቦችን የታደጉት የጌታ እግዚአብሔርን ክንዱ በማሰብ ነው።

ጌታን ተመለስልን እንዲገና አስበን የሚለው ቃል ንጉስ ዳዊት እንዳደረገው ከሕዝቡ የሚቀርበው ሀገርና ሕዝብ በክፉ መንገራና በጭንቅ በተያዙበት ወቅት መሆኑ ዛሬ ይስተዋል ይተግበር።

ንጋቱ ሲያቅላላ አጅግ ጥልቅ በሆነበት ሰዓት የአሰራኤል አባት ራሱም ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ትርጉም ያለው ስም የያዘው ያሰቆብ የጌታን መነካት ያገኘበት ጊዜን ያስታውሳል።

"በዚያችም ሌሊት ተነሳ ... ያሰቆብ ግን ለብቻው ቀረ አንድ ሰውም አሰነ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር ... ሊነጋ አቅላልቷልና ልቀቀኝ አለው አርሱም ካልባረከኝ አልለቅህም አለው ... በዚያም ሰፍራ ባረከው" *(ዘፍ.32÷24)*

በብርቱ ጸሎት አንድ ልዩ ተፈላጊ ነገር እግዚአብሔር አዘጋጅቷል። በዘመናትም በዚያ መንገድ ብቻ ጌታ ሥራውን በአማኝ ልጅቹ አየሠራ መንግሥቱን አስፍቷል ሕዝቡን ነክፉ መከራ ታድጓል። ከአለማችን ነፍተኛ ጥቅም የሚሰጡ ግኝቶችን አቀዳጅቷል።

ያ ልዩ ተፈላጊ ጉዳይ ደግሞ የእግዚአብሔር ሰዎች በራሳቸውም ሆነ በማንኛውም ነገር ላይ መታመን አቁመው በእግዚአብሔር ብቻ በመታመናቸው ነው።

ዛሬስ በሀገራችን ኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ በአማኝ ማኅበረሰብ ከቤተክርስቲያኑ እግዚአብሔር ነንዴን ኪገልጥ፣ ኪመክስ፣ ኪፈውስ የሚችለው በምን መንገድ ይሆን? አንቂ ንግር በፍጹም ሚታለያ መሆኑን ከአሜሪካ አስከ ኢትዮጵያ አይተናል። ብቸኛው መፍትሔ በጌታ ብቻ ታምኖ መጸለይ ነው።

ዛሬ እጅግ የሚያስፈልገን የተሰበረ ነገር ግን የተሞላ ጽዋ/ዋንጫ ነው

(በሚሊዮናዊ ጅናታን ጎፎርት)

እግዚአብሔር ዓለምን ነፈጠራት ጊዜ ጀምሮ ነብሩን በታላቅ መንገድ በገለፀባቸው መጠቀሚያዎቹ አማኞች በትህትና በተሰበረ ልብ ፊቱን በሚሹ የበረከቱ ዋንጫ ወይም ጽዋ በሆኑ ሰዎች ነው።

ሙሴንም ሆነ ኤርሚያስን ጌታ ከሥራው በጠራቸው ጊዜ ሁለቱም ብቃት አንደሌላቸው በተሰበረ መንፈስ ቢናገሩም ጌታ የሚፈልገው ያን የተሰበረ ልብ ስለነበር በታሪክ ያልታየ የዓርነት የነጻነት መልክተኛ ሆነው በባርነት በምርኮ የተጋዘውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ነጎብጽና ነባቢሎን ባርነት ከማወጣት የመሪነቱን ስፍራ ወስደዋል።

ዛሬም ጌታ አልተከወጠም በዚህ እጅግ አርኩሰት ጥላቻ ወንጀል ዘረኝነት ግድያ መናናቅ በቤተመቅደሱ ጭምር በሰፈነበት ወቅት ጌታ የሚፈልጋቸው አንደሙሴና ኤርሚያስ የተሰበረ ልብ ያላቸውን የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋዮችን ነው።

ይህ የተሰበረ ልብና ትህትና ነአንደበት ያለፈ በተግባር በፍሬ የሚታይ ነው።

በጨካኝ ኮሚኒስቶች ሳይበገሩ በመከራና በስቃይ የወንጌሉን ቃል ጠብቀው ከዚህ ዘመን ያደረሱ ዎች ማኒን የመሰሉ የቻይና ክርስቲያኖችን በሚሲዮናዊነት በወንጌል ያገለገሉ ጅናታን ይዘን የእግዚአብሔር መገልገያ አቃዎች የሆኑትን ትሁት አማኞች የሚገለጸው በተጨባጭ ካለፈበት የወንጌል አገልግሎት በመነሳት አውነተኛ ምስክርነቱን ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያም በዚህ አስከፊ የወንጌል አማኞች የስደት ዘመንም ሆነ ዛሬ ነበሔመንግስት አስከ ቤተመቅደሱ አጭበርባሪዎች በፈጣሪም ስም ሕዝባችንን በማሳሳት ከአርስ በርስ አልቂት በየተራ የሀሰት ትርክት በሚዘሩባት ምድራችን የተሰበረ ልብ ያላቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች እጅግ ያስፈልጉናል። አታላዮች የጌታ ቁጣ በአናንያና ሰጲራ ላይ የደረሰው ሳይመጣባችሁ ንስሐ ግቡ ተመለሱ ሁላችንም እንመለስ።

የትሁት የጌታ ታማኝ አገልጋይ ተርጓሚው በአካል ያገኛት የምጽአቱ የምስራች አገልጋይ የኩዊስ ለተኪ ምስክርነት

በ2002 ተርጓሚው ኑሮውን በአሜሪካ በጀመራበት ወቅት በኢንዲያና የሳትመት ቢሮ አስተባባሪ የነበረች አሳት ኩዊስ ወደጌታ አቅፍ ነመግባቷ በፊት የሚነተለውን የትህትና ሕይወቷ የሚመሰክረውን አነፍላለች።

በጠንቱ ለሚባሉን ጊዜያችን ብርቱ ምክር

ሕይወታችንን ለሰጠን በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ መከራና ሞት በትንሳኤ ያዳነን እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው።

ዓለማችን በአርኩሰት ነመሞላቱ ገና በክርስትናው ዘመን ጅማሬ በክርስትናው ዘመን ጅማሬ ጌታ በዮሐንስ ወንጌላዊ በኩል የሰጠን ራእይ ዛሬም አልተለወጠም አጅግ ብሰበታልና በብርቱ ሰምተነው መልእክቱን ለሁሉ አናስተላልፍ።

ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተነገረው የተግሳጽ መልእክት ለዛሬዋ ቤተክርስቲያን አጅግ በጠነከረ ሁኔታ ኪነገር ኪወሰ የሚገባ ጉዳይ ነው።

"የመጀመሪያ አምነታችንን አስነ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዩና ሆነናልና" *(ዕብ.3÷14)*

የዘመናችን የክርስቲያኖች ራስ ወደጅነትና ስንፍና የኃጢያት ብዛት ማለመሰል ዘፋኝነት ቀማኛነትና ነባለም ጋር መመሳሰል አጅግ ኪያሳፍረንና ልንናዘዝ ልንስተሳከል የሚገባበት ወቅት ላይ ነን። በዚህም ብቻ አንደተገባልን የተሰፋ ቃል ስንገኝ የክርስቶስ ተካፋዮች አንሆናለን። (2ጢሞ.3÷16)

የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈልን አንድንስተሳከል አንድመለስ አንድንሻሻል አንድንነቃቃ ለለሆነ በዚህ የምጽአቱ የምሥራች ሆነ በትክክለኛው መንገድ የሚሰጡ ስብከቶችና ትምህርቶች በቃሉ ለመስተሳከል በመመለስ እንዘጋጅ።

ለጸሎት ብንሰንፍ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል አናጣለን፣ ለመርገምና ለቁጣም አናደርጋለን። ብንመለስ ግን በምድርም በሰማይም ለዘላለም እንባረካለን (ኤፌ.1÷3)

የጸሎት ሕብረቶችንን አናበረታታ

ጌታችን ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል ብሎ ያስተማረንና ሐዋርያቱም ሳታቋርጡ ጸልዩ ብለው ያስጣሩን በጸሎት የሚገኘውን ድል የሚያረጋግጥ የታመነ ቃል ነው።

ስለዚህ ክርስቲያኖች በተለይ አገልጋዮች ሌሎችን ጉዳዮች ከመፈጸማችን በፊት የጌታን ፊት በግላችንና ከሕዝባችን ጋር በጸሎት እንፈልግ (ኩቃ.19፥46፣ 1ተሰ.5፥16)

ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ፍቅር ከሰሜት ያለፈ ዘላለማዊ ሰጦታ ነው

(በቻርለስ ፊኔ በአሜርካው የታላቁ መንፈሳዊ መነቃቃት ሰባኪ)

የእግዚአብሔር ትእዛዛትና ሕጎች የምሕረት ወንጌሉ ጭምር በእንዱ መለኮታዊ ባህሪይ ይጠቃለላሉ። ያም ቃል ፍቅር ይባላል።

በምዴራችን አዴግ ትርጉም የተዛባበት ቃል ቢኖር ፍቅር ሲሆን የፍቅር ትክክለኛው ትርጉም ግን ዘላለማዊና ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር በልጁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገለጸው ወንጌላዊ ዮሐንስ በሚገባ በመልእክቱ የገለጸው "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" (1ዮሐ.4፤7) የሚለው ነው።

ፍቅር ስሜትን የሚነካና በስሜትም የሚገለጽ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ያገኘነውና ከሌሎች እንዱናካፍለው የሰጠን ፍቅር ግን የሰዎች መጥፋት፣ ወዯ ገሀነም መነዲት ግዯ ብሎን ይድኑ ዘንዴ ከዚህ ጌታ እግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ የምንመሰክርበት፣ የምንጸልይበት፣ የምንሰብክበትና የምንንከባከብበት የአገልግሎታችን ዋነኛ መሠረታዊ ምንጭና መለኪያ ነው።

በአገልግሎችን የተፈለገውን ያህል ብንጥር ብንዴክም ብንተጋ ፍቅር ከሌለን በዴን፣ የብረት የጸናጽል ኳኳታ መሆኑን ሐዋሪያው በመልዕክቱ ይመክረናል። *"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ አንዯሚጮህ ናስ ወይም አንዯሚሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኛለሁ"* (1ቆሮ.13፤1)

በዚህ ወቅት በዓለማችን ዙሪያ በጌታና በሐዋሪያቱ አስቀዴሞም በነብያቱ የተነገረው የመጨረሻ ዘመን የእግዚአብሔር ጉብኝት የተዯናቀፈው ይህ የእግዚአብሔር ልዩ ምልክት ፍቅር ስሙን በተሸከምነው አማኞች ዘንዴ በመጥፋቱ ነው። አንዯመ ወይም አንዴ ጸውሎስ የወገኖቻችን መጥፋት ግዴ ቢለን በሀገራችን ሰው አንቅፋት ሲመታው አኔን ብሎን ከመውዯቅ ከመትረፍ አንዯሚተጉት በሆንን ነበር። (ዘኁ.11፥15፣ ሮሚ.9፥2)

እግዚአብሔር አራሱ ተገለጸበት ይህ ፍቅር አኛም የአርስ በርሳችን መለያ አንዯሆነ ጌታችን የገለጸው ፍቅር ምሕረት አውነትና ፍትህን ያቀፈ ነው።

ፍቅር በምሕረት አንዴተሞላ ወይንም ምሕረት የፍቅር መገለጫዎች ውስጥ ዋነኛው መሆኑን የምናውቀው በእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ የአዲም ዘር በጥፋቱ ዘላለማዊ ቁጣ የተገባው ምሕረትን ከእግዚአብሔር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመሰቀል የመከራ ሞቱና ትንሳኤው የተገለጸበት ልዩ ፍቅሩ ነው። ይህንን ፍቅር ያላስተተ ማንኛውም ዴክትሪን፣ ስብከት፣ የዝማሬና አገልግሎት የእግዚአብሔርን ዋነኛ መገለጫ ባህርይ ያጣ ሆኖ ማንንም የሚያዴን ይልቁንም የመረገም ውጤት አንዯሆነ በክርስትና ስም ለዓለም ዙሪያ በሀገራችን ኢትዮጵያ ጭምር በአስመሰይ በአታላዮች በተሸቀጠ በሀሰተኛ ማንነት የሚሳሳዱ ቅስቀሳዎች ያስነተሉት አስነፊ መተላለቅና የዘር ፍጅት ማስረጃ ነው።

አውነትና ፍትህ ያልተገለጡበት ክርስትናና ቤተክርስቲያን የፍቅር ሊባል የማይችል የዴራማ ወይም የማተኮያና የጥፋት ነው። አውነት አየተገለጠ ፍትህ ለሰው ልጅች አየተነፈገ አንዱ ዘር ከሌላው የተሻለ የበረታ የጠራ ተብሎ በተቀዯሰው የጌታ ቤት ሳይቀር የሚጠራበት ፍቅር ሊኖር ነቶ አይችልም።

አንዯዚሁም ፍትህ ለሁሉ ሳይጠበቅ ፍርዯገምዴል ፍርዴን በይፋና በስውር አየተመለከትን ፍቅር ነው ብንል የባሰብን ሐሰተኞና ኃጢአተኞች ሆነን አንቀራለንና። የእግዚአብሔር ፍቅር አንዲገለጥብን በንስሐ በጸሎት ቃሉን ተስትለን የአውነት የፍትህ ሰዎች ሆነን ራሳችንን ቤተሰባችንና ሀገራችንን አናዴን የሳለመ መከራ መፍትሔም አንሁን። የእግዚአብሔርን ፍቅርን ማስመሰልና መከለከል የከፋ ኃጢያት ነውና ዛሬውኑ ንስሃ ገብተን ጌታ በምህረቱ ትክክለኛ መንፈሳዊ ተሀዴሶና መነቃቃት የሚያስገኝልን ሕይወት አንጀምር።

የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት
የኢትዮጵያ ተጠሪ አልማዝ አሳየ
የፖ.ሣ.ቁ 8986፣ አዲስ አበባ

ወርቅ በአሳት እንዯሚፈተንና እንዯሚለይ ባለፉት ዘመናት በሀገራችን ኢትዮጵያ በተፈራረቁ መንግስሥትና ዛሬም ዴረስ በክርስትና ሽፋን አዴግ በዯሎች ዘረኝነት መሰፋፋቱን በጎ ህሊና ያለው ይረዯዋል። ሆኖም ግን አነዚህ በወንጌልና በክርስትና ካባ የተከፈሱ አሳሳቾች ክፉ ነገር የሚለይና ቅዴስናን የሚያረጋግጥ ሁኔታ ሲመጣ የተዯበቁበት ዘረኝነት ባለማዊነት በይፋ ሲገለጥ አያየን ነው።

የቆመ የሚመስል እንዯይወዯቅ ይጠንቀቅ ነውና ከአነዚህ ተምረን በወንጌሉ አውነት ተለይተን እንኑር። (1ጴጥ.1፥7፣ 1ቆሮ.10፥12)

የምሕረት አምባ አገልግሎት በኢትዮጵያ ጥሪ

አናፍ አመንሲሳ
አዴራሻ፡- ቄራ፣ አዲስ አበባ
ስልክ፡- 0913377328

"አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን ባገኘን በታላቅ መከራም ረዲታችን ነው።" (መዝሙር ዯዊት 46፥1)

እግዚአብሔር መሸሸጊያ የምሕረት አምባችን በሕይወታችን የተገለጠ ባለቤቴ ፋንታዬ ግርማና እኔ

አስተባባሪው ከሀገር ቤት ጀምሮ በልዩ ልዩ ምክንያት በስራና በትምህርት ሰበብ በውጭ ሀገር የሚሠማሩትን ስንደግፍ ቆይተናል።

በተለይ ባለፉት ዘጠኝ አመታት ከእነዚህ ወገኖቻችን ውስጥ በመካከለኛው ምሥራቅ በሥራ ሰበብ ተታለው በስፍተኛ ስቃይ ውስጥ የገቡት የዕርዳታ የድረሱልን ጥያቄ በየጊዜው ይደርሰናል።

ከሳኡዲ የተባረሩትም በደረሰባቸው አስከፊ ሁኔታ የተባረሩ ከIOM ጋር በመተባበር መልሰው እንዲቋቋሙ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲያችን ተሳትፈናል። ቀደም ባለው ጊዜ ከየመን ወደ አሜሪካ ከገቡት ቤት ትምህርትና ሥራ እንዲያገኙ ተሳትፈናል።

ሆኖም ግን ችግሩ እየተባባሰ በመምጣቱ ባለንበት ስቴት የሚገኘው የፍቅር ባለም አቀፍ አገልግሎ (Love Justice International) ትብብር ስለጠየቀን በሀገር ቤት የምሕረት አምባ አገልግሎት የተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት አዋቅረን አገልግሎቱን ቀጥሏል። ድርጅቱ ከተቋቋመ በአንድ ዓመት 350 ወገኖቻችንን ከአታላይ አስተላላፊ ሕገወጦች ተርፈው በሰላማዊ ሕይወት ከመሰማራት በቅቷል።

ይህን አገልግሎት የአንግሊዝኛ አትም በመጽሐፍ ቅዱሳት በትንሽ መደገፍ የጀመረ ሲሆን በዚህ ወር ነሐሴ 2015 ዓ.ም የጸሎት ማስታወቂያውን በባለም ዙሪያ ከሚገኙ ከ100 ሺ በላይ ከሆኑ የጋዜጣው ተሳታፊ አባላት አስታውቋል።

ስለዚህ የአማርኛው አትም አንባቢዎች፣ ይህንን ወገኖቻችንን የባህርና የበረሃ አሸዋ ሲሳይ ከመሆን፣ ከፎቅ ከመወርወር፣ ከጸታዊ ጥቃት፣ ከአካል ብልት ስርቆትና ከጉልበት ብዝበዛ የመታደግና ቀድሞ የሚደን ሥራ ላይ የተሰማራውን የምሕረት አምባ አገልግሎትን በጸሎት፣ በገንዘብና በሚቻላችሁ ሁሉ እንድትደግፉ አደራ እንላለን።

የአገልግሎቱ የኢትዮጵያ ፕሮጀክት ኃላፊ ወንድማችን አናፍ አመንሲሳን በስልክ ቁጥር 091337732 ማግኘት ትችላላችሁ።

አስተባባሪ አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቴ መላሻ

በመላው ባለም በክርስትና ስም መልካም ምግባር ያደረጉ እንዲሁ ሁሉ በዕርዳታና በተቸገሩት ስም ምዝበራ የሚያካሂዱ የታረዙትን ዕርዳታ ከግል ጥቅምና ምቾት የሚያውሉትን ህዝቡ ሊያጋልጥ ሊያወግዝ ይገባል።

በዚህ መልካም ሥራ የሚተጉ የመቂያንያው ሚንያምና ከእንግሊዝ ሀገር መጥታ በባህርዳር የተጐዱ ልጅችን የምትንባበበዋ ሴት በመልካም ምሳሌነት ከሚጠቀሱ ጥቂቶች ናቸው።

እኛ ግን እንደ አግዚአብሔር ቃል በየምጽአቱ የምሥራች አሳታሚዎች መኖሪያ እንደየነው በጭምትነት እንደ ጳውሎስ በድንኳን ጌታን ሕዝቡን አገልግሎ እንላለን (ሐዋ.18፥3)

የጸሎት ርእሶችና ማሳሰቢያ

የአማርኛውን ትርጉም በመዋጨ ድጋፍ መጥፋት በየጊዜው ማዘጋጀት ስላልቻልን የምትሉትን ከኢትዮጵያ ተጠሪ አልማዝ አሰየ የፖስታ ቁ. 8986 አደስ አበባ በመላክ ተባበሩን።

ከካናዳ

የምጽአቱ የምስራችን በቋሚነት ስለምትልኩልኝ ካመሰግን አወዳለሁ መልእክቶቻቸው ሕይወቴን የቀየረ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ቀጥሉበት።

ከመካከለኛው ምሥራቅ

የምጽአቱ የምስራችን በየጊዜው ስለምትልኩልኝ ጌታ የተመሰገነ ይሁን ከመጀመሪያ ጊዜ ባለፈው ዓመት መጀመሪያ ላይ ያገኘሁት አትም አስደናቂ ማበረታቻ ከሕይወቴ አስገኝቶልኛል። ብዙዎች በወንጌል አምነት በስደት በስጋት ላይ ባሉበት በዚህ ካለነው ጸሎት አድርጉልን።

ከዩጋንዳ (አፍሪካ)

ከሃያ ዓመታት በመላክ ላይ ስላላችሁት የምጽአቱ የምሥራች እጅግ አመሰግናለሁ። ከብዙ ውድቀት ያተረፈኝ መልዕክታችሁ በጣም ጠቅሞኛል ተባረኩልኝ።

ከሴሬላንካ

በተለያዩ የምሥራቃውያን ኃይማኖቶች ከተሞኩት ወገኖቻችን የወንጌሉ ብርሃን እንድናደርስ የሚያተጋን የምጽአቱ የምስራች ጌታ የተመሰገነ ይሁን አናንተ አዘጋጅቹንም ይባርካችሁ።

ከአውስትራሊያ

የምጽአቱ የምስራች መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ እንዲጠና የረዳኝ የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ ስለሆነ መላኩን ቀጥሉበት።

ከደቡብ ኮርያ (እስያ)

የምጽአቱ የምስራች ከመንፈሳዊ ሕይወቴ ማደግና መጠናከር ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገ የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ ነው። በሚቀጥለው ወር ያቅሜን ከደሞዜ ስጦታ ከመላክ ወሰናለሁ።

የሀገራችን ኢትዮጵያ የጸሎት ሀብረቶች

ካንኑሱ ዘመን ጀምሮ ወንጌል አማኞች እየተወገዙ እየተሰደዱ ከዛሬው ዘመን ደርሰዋል። በዚህ ሁሉ ግን የወንጌል አማኞችን ብርቱ ያደረጋቸው ዘመናዊ ትምህርት

ወይም ኬኮቹ አንዷሚነሱት የምዕራባውያን የሚሲዮናውያን ድጋፍ ሳይሆን የታመኑበትን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በጸሎት መጠየቃቸው ነው።

በደርግ የስዩቱ ዘመን በፍርሃት በጭንቀት በየመሥሪያ ቤቱ የነበሩት የጸሎት ኅብረቶች ብዙዎቻችንን የደገፉና አደሶችን በጌታ አንዷሚያምኑ ያደረጉ ነበሩ።

በየኮኬቹ የነበሩትም የጸሎት ሕብረቶች ትልቅ የጌታ ሥራ ታይቶባቸዋል። ስለዚህ ዛሬም የሀገራችን ቀውስ በነፋበት ወቅት በጸሎት ሀብረቶች በአውነት አንትጋ። (ማቴ.18፥20፣ ኬፌ.3፥12)

ምስጋናና ምስክርነቶች

የመጀን ምክሮች

መጽሐፍ ቅዱስን ነዮሐንስ ወንጌል ጀምሮ በጥሞና ማንበብ፤

በአቅራቢያ በሚገኝ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አማኝ ማህበር ጋር መቀላቀል።

ከአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምስራችን የአንግሊዝኛ አትም ባለቤቱ በሕይወት ሳሉ ይከታተሉ ነበር። ከአስተባባሪና ተርጓሚው ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴም ወዳጅ ነበር፤ አጅግም በረከቱን መስክሯል።

ከአገልግሎቱ የሚቻቸኝን መዋጮና ድጋፍ ከመላክ አሞክራለሁ። የአማርኛውን ትርጉም ላኩልኝ።

ከጂንካ ደቡብ፣ ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምሥራች ነኒቤተሰቤ አጅግ የጠቀመን መንፈሳዊ ምግባችን ነውና መላኩን ቀጥሉ አንፀልይላችኋለን።

ከመቱ፣ ምዕራብ ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምስራች ከወንጌል አገልግሎት መጣም አየረደን ነው። ሳታቋርጡ ቶሎ ቶሎ በመላክ ተባበሩን ጌታ ይባርካችሁ።

ከአዲግራት፣ ሰሜን ኢትዮጵያ

ነብዙ ጊዜያት በኋላ የምጽአቱ የምሥራች በማግኘታችን በጣም ደስ ብሎናል። ጌታ ከአገልግሎታችሁ መነናወን ይስጣችሁ።

ከባቢሌ፣ ምስራቅ ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምሥራችና የአዲስ ኪዳን በወንድማችን ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ የተላከ ከአገልግሎታችን ብዙ ጠቅሞናል። በዚህ ላለን ዛቻው ማስጠንቀቂያው ከበዛብን በብርቱ ጸልዩልን።

ከጋና፣ ምአራብ አፍሪካ

ወጣት ፓስተር ሆኜ በአገልግሎት ስለረዳኝ የአንግሊዘኛ ስለ የምጽአቱ የምስራች ጌታን አመሰግናለሁ።

ከፊሊፒንስ፣ አስያ

ስለሚያበረታታን ስለሚያንጸን የምጽአቱ የምሥራች አናመሰግናለን ተባረኩ።

ማሳሰቢያ ለአንባቢዎች

ከሁላችሁም ለመመለስ ጊዜና አቅም ስለሌለን በዚሁ አምዱ ምስጋናችንን አናቀርባለን፣ አስተባባሪው።

ጌታችን ለሕዝቡ የሚለዩበት ጸሎት

(በቻርለስ ስፐርጅን (1834-1892))

"በአውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ አውነት ነው" (ዮሐ.17፥17)

የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ጌታ ለሕዝቡ ያቀረበው የምልጃ ጸሎት ነቅዱሳት መጽሐፍት የቅዱስ ሁሉ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል። ለምን? በዚህ ጸሎት ራሱ አምላክ የሆነው የአምላክ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነአግዚአብሔር ጋር ያለውን ፍጹም አንድነትና ፍቅር በሚገልጽ መልኩ የቀረበ ስለሆነ ነው።

ጌታችን ሕዝቡ አደቀደለለት ነምንም ነገር በላይ ይፈልጋል። የአግዚአብሔር ሕዝብ የሚቀደሰው ወይም የሚለየው ደግሞ በአውነት ብቻ ነው። ስለቅድስና መልካም ወይም ልዩ ምሳሌና ፈጣሪነቱ ነአግዚአብሔር በላይ ምንም የለም አርሱ ቅዱስ የተቀደሰ የተለየ ነውና።

በዚህ ልዩ በሆነው ቅድስና መለየት ነኃጢአት፣ ነውድቀት፣ በስንፍና በትዕቢት በአርኩሰት መቀደስ መለየት የበለጠ ምን ልዩ ዘለለማዊ ነገር ይኖራል? ጌታ ነክፉ ጠብቃቸው ያለው አማኞች ነክፋው ሰይጣን ሥራ አንዲርቁ ነው።

ክርስቲያኖች በዓለም ቢኖሩም በዓለም አንዳልሆኑ ጌታ ያስተማረው በዚህ በአንግድነት በምንኖርበት ዓለም ክርስቲያኖች የአግዚአብሔርን ቅድስና በህይወታችን በንግግራችን በስራዎቻችን አንድናሳይና ሰዎችን ነጠፊዋ ዓለም አንድናተርፍ የአግዚአብሔር መሣሪያ ለመሆን ነው (ዮሐ።17፥15)።

በዓለም ዙሪያ በአፍሪካም ይሁን በአሜሪካ በአውሮፓና በአስያ ያለን አማኞች በዓለም መኖራችን የአግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን ባለንበት ዓለም የአግዚአብሔር ወኪሎች መሆናችንም የአርሱ ፈቃድና የአኛ የተሰጠን ኃላፊነት ነው።

ዓለም በክፉ አንደተያዘ አኛም በዚህ ክፉ ዓለም በራሳችን ምርጫ ሳይሆን በአግዚአብሔር አንደተጠራን አንደተመረጥን ቅዱስ ቃሉ ያስተምረናልና በዚህ ጸንተን የአግዘአብሔርን ቅድስና በጸሎት በቃሉና በሕይወት አንዲያኖረን ከአግዚአብሔር ዘወትር ጸሎተት አናቅርብ።

የምጽዓቱ የምስራች የወንጌል አገልግሎት

አሳታሚ ሬክ ነርማይክል
ተርጓሚ አስተባባሪ ኤዲ መካሻ
የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ

አሪ በይ ሀገሬ ኢትዮጵያዬ!

የደቡብ አፍሪካው የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ የትግል አጋሮች ጸጸስ ዴዝሞንድ ቱቱና ቄስ አለን ፓተን ያደረጉት አስተዋጽዖ ከተገቡ ሕዝቦች ከሚታረዱ ሰዎች በዘራቸው ምክንያት ከሚሰደዱ ከሚፈናቀሉ የመንፈሳዊ መሪዎችን ታላፊነትና ተዋጽኦ ያስተምራሉ።

ባለመታደል ግን ሀገራችን ኢትዮጵያ ነአጼዎቹ ዘመን ጀምሮ ምንደኛ የኃይማኖት መሪዎች የበቀሉባት ሆና በሰዎች ላይ የሚደርሱ ግፎችን በመቃወም ነገሥታቱን ፕሬዚደንቶቹን ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ወይም የክልል የክፍለ ሀገርና የጠቅላይ ግዛት መሪዎችን ነመገሰጽ ይልቅ ከእነዚህ ክፉ መሪዎች ያደገደጉ መሆናቸው አጅግ በጣም ያሳዝናል።

በዚህ ሰዓት በሀገራችን የሚታየውን ግፍና የዘር መድሎ ከማውገዝ ዋነኛ ምሳሌ መሆን የሚገባቸው መንፈሳዊ መሪዎችን ይቀሰቅስ ዘንድ የደቡብ አፍሪካ የነፃነቱ ትግል አጋር የቄስ አለን ፓተን አሪ በይ ሀገሬን ወደ አማርኛ የተረጐሙት የደራሲያን ማህበር መስራች አቶ አማረ ማሞ ዘወትር ይታሰባሉ።

ወቅታዊ አሪ በይ ሀገሬን የወገኖቻችን የተገፉት የታረዙት የሚጨፈጨፉት ጉዳይ ከሚገደን ልሳን በመሆን የሚቀጥለውን ሥነግጥም አቀርባለሁ።

አሪ በይ ሀገሬ፣ አሪ በይ ኢትዮጵያ!

(መዝሙረ ዳዊት 68፡31)

ነጥንት ነመሠረቱ በታሪክ በመጻሕፍቱ
የተጠራች ታላቅ ሀገር የአፍሪካ መሠረቱ
የሰው ዘር መገኛ የኢትዮጲስ አትብቱ
በብሉይ በሐዲስ የተወሳች ቀዳሚቱ
ኢትዮጵያ ሀገሬ ምነው ተዋረደች
በዓለም የስደት የመከራ ምሳሌ ሆነች
በማያልቅ የርስ በርስ ጦርነት ደኅነመች
ብዙ ሚሊዮኖችን ዛሬም አስራበች
የአፍሪካ ምሳሌ ስትሆን ማፈሪያ ሆነች
አሪ በይ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ሀገር
የሥልጣኔና የሰው ዘር መገኛ ሠፈር
የሚሰማ ፈጣሪ አለሽ በቃል የሚናገር
አጅችሽን ፈጥነሽ አንሺ የሚል ቸር
በመዝሙረ ዳዊት በአዲስ ሳይቀር
ያ ብቻ ነው መፍትሔሽ አናት ሀገር
አሪሬ በይ ከፈጣሪ መከራ ግፍሽ አንዲያጥር
በሀገርም በውጭም ያለን አንተባበር
ለሁሉ ቻይ ጌታ በጸም በጸሎት አንንገር።